20ኛ ዓመት ቁጥር 3
20th Year No. 3

ባሕር ዳር ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም
Bahir Dar, November 07, 2014

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 50 ብር
Unit Price Birr 50

| ማውጫ | Content |
|---|---|
| **አዋጅ ቁጥር 222/2007 ዓ.ም** | **Proclamation No.222/2014** |
| **የተሻሻለው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ** | **The Amhaa National Regional State Revised Executive Bodies Establishment Proclamation** |

## አዋጅ ቁጥር 222/2007 ዓ/ም

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግስት ኢኮኖሚያዊ አቅሙ በፈቀደ መጠን የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያላሳዳጊ የቀሩ ህፃናትን የማቋቋምና የመንከባከብ ሀላፊነት እንዳለበት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ /41/ ንዑስ አንቀፅ /5/ ስር የተደነገገ በመሆኑ፣

ይህንኑ ህገ-መንግስታዊ ሀላፊነት በሚገባ ለመወጣት ያመች ዘንድ የዘርፉ መስሪያ ቤት የሆነውን የክልሉን ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ስልጣን ከተጠቀሰው ተልዕኮ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

## Proclamation No.222/2014

## A proclamation Issued to Ammend the Amhaa National Regional State Executive Bodies Establishment Proclamation

WHERE AS, the provision stipulated under sub-article /5/ of Article /41/ of the constitution, the Regional Government, shall have aresponsibility to establish and care the physical and mental disabilities, old ages and orphan children, as its economical power;

WHERE AS, it has been found necessary to strengthen the power of regional labor and social offairs Bureau in relation with the indicated mission, that shall enable to discharege its constitutional responsibility properly;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ /49/ ንዑስ አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " የክልል አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 222/2007 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም ከዚህ እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፡-

በአዋጁ አንቀፅ /27/ ስር ከንዑስ አንቀፅ /9/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ /10/ የገባ ሲሆን በስራ ላይ ያለው ንዑስ አንቀፅ /10/ በዚህ ማሻሻያ መሠረት ንዑስ አንቀፅ /11/ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

/10/ በስራ ላይ ያሉትን የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ፣ ተሀድሶና እንክብካቤ ማዕከላት ያስተዳድራል፣ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እንደተገቢነታቸው መሰል ማዕከላትንና ድርጅቶችን ያቋቁማል፣ ዝርዝሩም በህግ ይወሰናል፡፡

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሄራዊ ክልልፕሬዚዳንት

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara Region, pursuant to the powers vested in it under Article /49/ sub-article 3/1/ of the Revised National Regional constitution, hereby proclaims this proclamation.

1. **<u>Short Title</u>**

This proclamation may be citad as "the Amhara National Regional State Executives Bodies Establishment proclamation, Revised proclamation No.222/2014."

2. **<u>Ammendment</u>**

The Amhara National Regional State Executive Bodies Establisment proclamation No 176/2011 shall be ammended by this proclamation as follows:

New sub-article /10/ is incorporated the following new sub –article /10/ is entered, next to sub –article /9/ under Article /27/ of the proclamation; the sub-article /10/ in effect, shall be changed into sub –article /11/ pursuant to this ammendment.

/10/ The particulars shall be determined by regulation, that shall be issued for the implementation of this proclamation; administer centers that are in effect of the old ages and the disabilities support, rehabilitation and protection; establish similar centers and organizations as deemed as necessary, in different places, of the Region;

3. **<u>Effective Date</u>**

This proclamation shall come into force, as of its publication date in the Zikre-Hig Gazzeettee of the Regional Government.

Done at Bahir Dar,

This 7th day of November, 2014

Gezdu Andargachew

President of the Amhara National Region